german cooperation
DEUTSCHE ZUSAMMENARBEIT

Implemented by:

giz Deutsche Gesellschaft für Internationale Zusammenarbeit (GIZ) GmbH

In cooperation with:



በደረቅ እና ከፊል ደረቅ በሆኑ ቆላማ የኢትዮጵያ አካባቢዎች (አፋር እና ሶማሌ ክልል) የአፈር መልሶ መቋቋምን ማጠናከር

# በኢትዮጵያ በረሃማ ስፍራዎች ለሚኖሩ አርብቶ አደሮች አሳታፊ የማህበረሰብ እቅድ የተዘጋጀ የፒአርኤ ዘዴ

## የቴክኒካዊ አፈጻጸም የስልጠና መመሪያ

የታህሳስ 2013 እትም

ይህ እትም የጀርመን ፌደራል መንግስት የትብብር እና ልማት ሚንስትርን በመወከል በጀርመን አለም አቀፍ ተራድኦ ድርጅት የተዘጋጀ ነው።

# ይዘት


የምስሎች ዝርዝር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4

1 መግቢያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5

2 ተሳትፎ: አይነቶች፣ አጋሮች፣ ልማዶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5

3 የገጠር ግምገማ የማህበረሰብ እቅድ ውስጥ አሳታፊ . . . . . . . . . . . . . . . . 7

3.1 አላማዎች እና ርመርሆች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 7

3.2 ባህሪያት እና መድሎዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 8

3.3 የዋና አቅድ ክፍል ሚና እና ተግባራት . . . . . . . . . . . . . . . . . . 9

3.4 ዘዴያዊ መሳሪያዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 10

3.4.1 በከፊል የተዋቀሩ እና የትኩረት ቡድን ቃለ መጠይቆች . . . . . . . . . 10

3.4.2 የሀብት ካርታ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 10

3.4.3 ወቅታዊ ምስል . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 12

3.4.4 ባለ ድርሻ አካላትን መመርመር፤ ቬን ዲያግራም . . . . . . . . . . . . 13

3.4.5 ውጤት እና ደረጃ: ችግሮችን እና መፍሄዎችን ቅደም ተከተል መስጠት . 14

3.4.6 የችግር/ የአላማ ዛፍ: ምክንያታዊ ትስስችሮን በመፍጠር . . . . . . . . 17

3.5 የግብረ መልስ ስብሰባ እና የማህበረብሰ የድርጊት መርሀ ግብር መፍጠር . . . . 18

3.6 ገደችቦ እና ስቶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 19

ጽሁፍ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 21

አባሪ 1: የዋና እቅድ ቡድን ሚና እና ተግባር . . . . . . . . . . . . . . . . . . 22

# ቁጥሮች ዝርዝር


ቁጥሮች 1: የተሳትፎ መሰላል (ከአርንስቴን የተቀሰደ, 1962) . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .5

ቁጥሮች 2: የአስተብባሪነት አስተዋጾ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .10

ቁጥሮች 3: የአስተባባሪዎች አመልካከት (ከቻምበርስ የተወሰደ, 2001) . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .10

ቁጥሮች 4: የመን፣ ለዝ እና ገዋኔ ወረዳዎች በኢትዮጵያ የሀብት ካርታ 1998 (የግል ምንጭ). . . . . . . . .15

ቁጥሮች 5: የለዝ እና ገዋኔ ወረዳ ወቅታዊ ግዜ መቁጠሪያ፣ 1998 (የግል ምንጭ). . . . . . . . . . . . . . .17

ቁጥሮች 6: ቬን ዲያግራም፣ የግል ረቂቅ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .19

ቁጥሮች 7: የለዝ እና ገዋኔ ወረዳዎች ችግር ደረጃ ማውጣት፣ 1998 (የግል ምንጭ) . . . . . . . . . . . . .20

ቁጥሮች 8: በብልሀት በማጣመር ችግሮችን ማነጻጸር (የፒአርኤ ስልጠና ውጤት, 2013) . . . . . . . . . . .21

ቁጥሮች 9: የማትሪክስ ደረጃ፣ የዚምባብዌ ምሳሌ (ስኮንስ 1994) . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .23

ቁጥሮች 10: የችግር ዛፍ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .25


# ምህጻረ ቃላት

| | |
|---|---|
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |

# 1 መግቢያ

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ የግብርና ሚንስትር፣ የተፈጥሮ ሀብት አመራር ዳይሬክቶሬት የሚመራው የማህበረሰብ እቅድ መዋቅርን አሳታፊ ሂደት አቅጣጫ ለማስያዝ የወጣ መመሪያ ነው:: የአለም አቀፉ የአፈር ጥበቃ እና ህክምና ለምግብ ዋስትና መርሀ-ግብር አካል የሆነው የአፋር አፈር ህክምና ፕሮጀክት የተዘጋጀ ነው:: አንዱ የአፋር አፈር ህክምና አላማ (ውጤት 1) የግጦሽ እና የእርሻ ሀብት አያያዝን በእራስ አገዝ የገጠር ሀብት ተጠቃሚዎች መምራት መቻል ሲሆን ይህም የአካባቢው ማህበረሰብ   ማህበረሰብ መር ልማት እንቅስቃሴች ውስጥ ዋነኛ አጋር መሆኑን የሚጠቁም ነው:: የተፈጥሮ ሀብቶች በዘላቂ መንገድ ለመጠበቅ በትግበራ ላይ ያሉ እርምጃዎች፣ በወረዳ፣ ቀበሌ አስተዳደር እና የአፋር ጎሳዎችን ያሳተፈ እቅድ ማቀድ እጅግ ጠቃሚ ነው::

የዚህ መመሪያ ዋና አላማ ሁለት ነው፤

1. አሳታፊ የማህበረሰብ እቅድ እና እላቂ የፕሮጀክት እንቅስቃሴዎች ከታች ወደ ላይ የሆነ ሂደት ዋና ሚናዎች ጠቃሚነት መሳየት፤
2. ለውጪያዊ አስተባባሪያዎች የዘዴያዊ እና ማህበራዊ አቅሞችን ለአሳታፊ የገጠር ግምገማ ዘዴ አግባባዊ ትግበራ የገጠር ማህበረሰቡ የአካባቢ እቅድን በተመለከተ ያላቸው አመለካከት፣ ልምድ እና እውቀት መገንባት ናቸው::

# 2. ተሳትፎ፤ አይነት፣ አጋሮች፣ ልማዶች

## ተሳትፎ ለምን? ምን አይነት ተሳትፎ?


መንግስታት ተጠያቂነት እንዲኖራቸው ብዙ አጋሮች የአርብቶ አደር ልማት በእቅድ አወጣጥ እና ውሳኔ አሰጣጥ ወቅት ግለሰቦች እና ቡድኖች እንዲሳተፉ ይመክራሉ:: አሳታፊ ሂደቶች በዜጎች እና የፖለቲካ ውሳኔ በሚያሳልፉ መካከል የቅርብ ግንኙነት እንዲኖር እና የእቅድ አወጣጡ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ እና በአብዛኛው መህበረሰብ የተደገፈ እንዲሆን ያደርጋል:: በልማት ትብብር ውስጥ ተሳትፎ የሚከሉትን መሰረት ያደረገ ነው፤

- መርሀ-ግብሮቹ ወይም ፕሮጀክቶቹ የአካባቢ አጋሮች አቅምን መሰረት ያደረጉ ናቸው፤
- በውጫዊ የልማት ባለሙያዎች የአካብቢ እውቀት እና ልምዶች ከግምት ውስጥ ገብተዋል፤
- የአካባቢ እና የውጪ ባለ ድርሻ አካላት ሀላፊቶችን ማጥራት እና መጋራት፤
- ዘላቂ ለውጥ ለማምጣት እና ሁሉም ባለድርሻ አካላት የፕሮጀክቱ ባለቤቶች እንዲሆኑ ለማስቻል የጋራ ቁርጠኝነት መፍጠር፤

የተሳትፎ ትርጉም እና ተያያዥ የሆኑ አሳታፊ ልማዶች በተለያዩ አጋሮች ዘንድ ይለያያሉ:: በቅርብ አስርት አመታት እየጨመረ በመጣው ታዋቂነት ምክንያት፣ መሳተፍ ድፍን የሆነ የተለመደ ቃል ሆኖ በራሳቸው ፍልጎት መሰረት የተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተለያየ ትርጉም ይሰጡታል:: በብዛት የመሳተፍን ትርጉም በተመለከተ ያለው አመለካከት በአሳታፊ ሂደቱ ላይ በተሳተፉ የተለያዩ አጋሮች ዘንድ የተለያየ ነው:: ስለዚህም፣ በእቅድ አውጪዎቹ እና አስተባባሪዎቹ ምን አይነት የማህበረሰብ ተሳትፎ አስፈላጊ እና የሚልቻ እንደሆነ መለትየ አለባቸው::

ከስር በምስል 1 የተገለጸው የአርንስቴን የተሳትፎ መሰላል ጠቃሚ የሆነ በአሳታፊ ሂደት ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ፍላጎትን መጠን ማሳያ ነው:: በተለያዩ ደረጃዎች ውስጥ፣ በውሳኔ እና በሀብት ላይ ያለ ቁጥጥር ከመንግስት ወደ ዜጎች ይዞራል:: የንግግር ተሳትፎ ምክክር እና መረጃ ተብሎ ስለሚወሰድ በልማት ድርጅቶች እና የመንግስት ባለድርሻ አካላት ጥረቶች ውስጥ ሰፊ ድርሻ አላቸው ተብሎ ይገመታል:: ዜጎችን ከማጎልበት ይልቅ የንግግር ተሳትፎ አስቀድሞ ሀይል ባላቸው አጋሮች የተወሰነ ውሳኔ ተቀባይነት እንዲያገኝ ብቻ የሚረዳ ነው (ለምሳሌ፣ የግድብ መሰራት ወይም የመስኖ ተፋስስ)::

ምስል 1: የተሳትፎ መሰላል (ከአርስንቴ የተወሰደ, 1962)




## ማን ምን ውስጥ ይሳተፍ?

ተሳትፎ እራሱን ቴክኒክ ብቻ ሳይሆን እራሱን የቻለ የፖለቲካ ሂደት ሆኖ መወሰድ አለበት:: የየራሳቸውን ፕሮጀክቶች ይዘው እና ማህበረሰቡን እንወክላለን ብለው የሚመጡ የተለያዩ አጋሮች የሚመጡ የሀይል ልዩነቶች እና ክርክሮች ላይ ድንበር ለማስመር ይጠቅማል:: የእቅድ ሂደትን ማን እንደሚያነሳሳ፣ ተሳታፊዎችን ማን እንደሚመርጥ፣ ማን ምን ላይ እንደሚሳተፍ እና ማን እንደሚቀር መጠየቅ ጠቃሚ ነው:: ብዙ ግዜ ሀይል ያላቸው ቁንጮ (ኤሊት) ቡድኖች እና ግለሰቦች ሂደቱን ሊቀሙ እና ህብረተሰቡን እንወክላለን በማለት ነገር ግን የማህበረሰቡን ባለድርሻ አካላት በማግለል የራሳቸውን ፍላጎት ሊገፉ ይችላሉ:: በሀሳብ ደረጃ፣ ጥልቅ (በሁሉም ልጣቃ ገብነቶች ደረጃ) እና ሰፊ (ሁሉንም ባለድርሻ አልላት ያሳተፈ) ተሳትፎ አይነተኛ አሳታፊ እቅድ ሁኔታን ሊፈጥር ይችላል፤ ነገር ግን፣ ይህ ብዙ ግዜ የማይልቻ ነው:: ጥሩ የተሳትፎ አይነት የሚያልመው፣ የጉዳዩን አላማ መሰረት በማድረግ ጥልቀት እና ስፋት ያለውን ተሳትፎ አመጣጥኖ በማስድኬ ላይ መሰረት ያደረገ ነው:: እውናዊነት በመጨረሻ በእቅድ ወይም በስብሰባ ላይ ማን እንደሚሳተፍ ይወስናል:: ነገር ግን፣ ሊሳተፉ የሚገባቸውን ባለደርሻ አካላት የመለየት ስራ ትልቅ ትኩረት ይገባዋል:: ሁሉንም ማህበራዊ ህብር የሚወክሉ ተሳታፊዎችን የመምረጡ ተግባር የአርብቶ አደሩን ማህበራዊ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልዩነት መረዳት እና የሚመለከታቸውን ሰዎች ለማነሳሳት በጥልቀት መሳተፍ ይስፈልጋል::

የተለመዱ ተሳታፊዎችን የሚያገሉ መንገዶች የሚከተሉትን፤ (ጊልፉስ፣ 2001):

- ተደራሽነትን መሰረት ያደረገ ማግለያ፤ - ቃለ-መጠይቁን ተረዳሽ ለሆኑ ሰዎች ብቻ ማድረግ (ለምሳሌ፣ በዋና መንገድ አቅራቢያ የሚኖሩትን መምረጥ);
- የደረጃ መሰረት ያደረገ ማግለያ - በማህበረሰቡ ውስጥ ቦታ ያላቸው እና መሪ የሆኑ ሰዎችን ማነጋገር፤
- ስርአተ ጾታ መሰረት ያደረገ ማግለል - ሴቶች የሌሉበት ተሳትፎ;[1]
- ልዩነትን መሰርት ያደረገ ማግለል - በማህበረሰብ ውስጥ ያሉ የተለይዩ ቡድኖች መወከላቸውን ያለማረጋገጥ (ለምሳሌ ብዛት ያላቸውን እና አነስተኛ ጎሳዎችን አለማመጣጠን);
- ወቅትን መሰረት ያደረገ  ማግለል - በአንድ  አንድ ወቅቶች የህዝቡ አንድ አንድ አካላት በቦታው ላይገኙ ይችላሉ (ተንቀሳቃሽ አርብቶ አደሮች፣ ተንቀሳቃሽ ፍልሰተኞች);
- የስራ ሰዓትን መሰትረ ያድረግ ማግለል - በስራ ቀን እና ሰዓት አብዛኛው የማህበረሰብ ክፍሎች አይገኙም፤
- ፕሮጀክትን መሰረት ያደረገ መድሎ - ቃለ-መጠይቁን በፕሮጀክት እና በተቋማት ላይ ለተሳተፉ ሰዎች ብቻ ማድረግ፤

ሰዎች ላለመሳተፍ እራሳቸውን ሊያገሉ ይችልሉ:: የተወሰኑ ቡድችኖ በእቅድ አወጣጥ ወቅት ግዜው እና ቆይታው ካልተመቻቸው ላይሳተፉ ይችላሉ:: ሌሎች ደግሞ ህዝብ ፊት መናገር ስለማይፈልጉ እና ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ሌሎች መርሀ-ግብሮች ላይ ስለተሳትፉ ተሰላችተው መሳተፍ ላይፈልጉ ይችላሉ:: የመጨረሻ ውሳኔ በሌሎች ከተሰጠ በኂላ በሚደረግ ስብሰባ ለውጥ ይመጣል ብለው ሰዎች ስለማያስቡ በመንግስት የሚካሄድ ስብሰባ እና ግምገማ ጥቅም የለውም ብለው ሊስያቡ ይችልሉ:: በዚህ መሰረት፣ ማንኛውም ኤጀንሲ ማድረግ የሚችላቸውን እና የሚችላቸውን ነገሮች ማወቅ መልቻ አለበት::

1 በትንሽ ቡድን ከተከፋፈሉ የሴት ቡድኖች ጋር በሴት አስተባባሪ አማካኝነት መወያየት ጠቃሚ ነው::

# 3.አሳታፊ የገጠር ግምገማ በማህበረሰብ እቅድ ውስጥ

## 3.1 አላማዎች እና መርሆች

አሳታፊ የማህበረብሰ ግምገማ ዘዴዎች የአካባቢውን ማህበረሰብ የውስጥ እይታ፣ ልዩ ልዩ አካባቢያዊ አመለካከቶች፣ አስተሳሰቦች እና እውቀት ማሳየት ይፈልጋሉ፡፡ አሳታፊ የማህበረብሰ ግምገማ ማለት የማህበረሰቡ አባላት ፍላጎታቸውን የሚመረምሩበት፣ መፍሄዎችን የሚለዩበት እና የሚያዳብሩበት እንዲሁም የድርትጊ መርሀ ግብርን የሚገመግሙበት እና የሚተገብሩበት ሂደት ነው፡፡ ብዙ ግዜ፣ ንፅፅራዊ መጠኖች፣ ውጤቶች እና ደረጃዎች ብቻ ለውሳኔ አሰጣጥ እና ተግባራትን ለማቀድ የሚያስፈልጉ ነገሮች ናቸው፡፡ የአካባቢው ማህበረብሰብ ለማብቃት ጥቅም ላይ የሚውሉ ዘዴችዎ ማህበረሰቡ የራሳቸውን ግምገማ እንዲያደርጉ እና የራሳቸውን ድምጽ እንዲያሰሙ እንዲሁም እርምጃ እንዲወስዱ ያስችልላ፡፡

አሳታፊ የገጠር ግምገማ ዋና መርሆች፤

- የሶስት ማዕቀፍ: መረጃዎችን ለማጎልበት እና ለማረጋገጥ የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም፤
- የሚና እና የሀይል ግንኙነትን መቀልበስ:
  - ከአካባቢው ማህበረሰብ መማር የሚፈልጉ የልማት ባለሙያዎችን እንደ አስተባሪዎች መመደብ፤
  - በአካባቢው ያለውን እውቀት መለካት
- በቡድን መማር፤ በተለያዩ ቡድችኖ መካከል ያለውን የተለያየ አመለካከት ማየት (ስርአተ ጾታ፣ ሀብት ወዘተ...)
- በቦታ የሚደረግ ምርመራ እና ማቅረብ
- በእይታ መጋራት፤ ውጤቶችን ለተሳታፊዎች ለውይይት እና ለድርድር ማጋራት፤
- ሆን ብሎ መተው፤ አላስፈላጊ መረጃዎችን መተው
- ከእይታ ጋር የተያያዙ ዘዴዎች ላይ ማተኮር
  - 'መሬት የወረደ ዴሞክራሲ': የተገለጸው በሁሉም መታየት፣ መዳሰስ፣ መቀየር/መንቀሳቀስ የሚችልበት፤
  - በመሬት ላይ የሚቀ;
- ተርታ ማስያዝ: እርስ በእርስ የሚተጋገዙ መሳሪያዎች መጠቀም፤

አርብቶ አደሮች ባለሙያዎች ተብለው የሚወሰዱ ሲሆን የልማት ባለሙያዎች ወይም ተመራማሪዎች ደግሞ ከአካባቢው ማህበረሰብ በአካብቢው ማህበረሰብ ጋር እና በአካባቢው ማህበረሰብ የሚማሩ ናቸው፡፡ የቡድን እይታ ሂደቱ የጋራ ውይይት፣ የመማር ሂደቶች እና የባለቤትነት ውጤቶች፡፡ የአሳታፊ ድርጊቶቹ ውጤቶች በዋና እቅዱ ቡድን እና በተሳታፊዎች በእይታ፣ በፕሬዘንቴሽን እና ውይይት አማካኝነት የማጋራት ተግባር ይከናወናል፡፡

መንገዶችን በብልሀት መምረጥ እና ተራ በተራ ማከናወን ዋነኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ የአሳታፊ ማህበረሰብ እቅድን አላማ የሚያሳኩ (በአፋር አፈር መልሶ ማቋቋም ፕሮጀክት፤ የአየር ንብረት ለውጥን በተላመደ መልኩ የተፈጥሮ ሀብትን በተሻለ መንገድ ለመምራት እድሎችን ለመለየት እና ) ፕሮጀክቶች ላይ ብዙ መንገዶችን ከመጠቀም ይልቅ፣ ስርአተ ጾታን መሰረት ያደረጉ ውስን መተግበሪያዎችን መጠቀም ይሻላል፡፡ በመሆኑም፣ በዚህ መመሪያ የተቀመጡት መንገዶች ለአፋር አፈር መልሶ መቋቋም ፕሮጀክት ሁኔታ ተመቺ ስለሆነ የተመረጠ ነው፡፡ ይህም የሚከተሉትን ይጨምራል፤

1. ሁኔታን ለመመርመር የሚረዱ መንገዶች: የተፈጥሮ ሀብቶችን ጠቀሜታ እና የቦታ እና የወቅት ስብጥር፣ ስርአተ ጾታ ተኮር የመሬት አጠቃቀም ሁኔታ እና አያያዝ ችግሮች (ተደራሽነት፣ የመሬት መኖር ወዘተ...)፣ የተቋም መኖር እና ግጭቶች
2. መርሀ-ግብሮችን ለማዘጋጀት የሚጠቅሙ መንገዶች፤ ችግሮችን መለየት እና ቅድሚያ መስጠት፣ እድሎች እና አቅሞች፣ እና ጠንካራ እና ማህበረሰብን መሰረት ያደረገ የመርሀ-ግብሮች ስትራቴጂ እና ተግባራት ሴቶችን እና ወንዶችን በእኩል ለሚያሳትፍ የተሻሻለ የሀብት ልማት፡፡


አሳታፊ የገጠር ግምገማዎች መንገዶች አሳታፊ የማህበረሰብ እቅድን ጨምሮ በተለያዩ መስኮች መጠምቀ ይቻላል፡፡

- የአሳታፊ የማህበረሰብ ልማት ሂደት ዝርዝር
- ማህበረሰብ መምረጥ እና የዋና እቅድ ቡድንን መመስረት፤
- የሎጂስቲክስ ዝግጅት እና የቅድሚያ ቦታ ጉብኝት፤
- ለእቅድ ሂደቱ የትግበራ እቅድ ማዘጋጀት፣ የመንገዶች፣ አላማዎች፣ ርእሶች፣ ሊፈጠሩ የሚችሉ ውጤቶች፣ አስፈላጊ ቁሳቁችሶ፣ በቡድኑ ውስጥ ያሉ ሀላፊነቶች፣ አስፈላጊ የሆነው ግዜ፤
- የእቅድ ሂደት፤
  - መረጃ ማሰባብሰ፣ መመርመር እና
  - ችግሮችን ደረጃ መስጠት እና መፍትሄ መፈለግ፣ ውጤቱንም ማቅረብ፤
  - በማህበረሰብ እቅድ ቡድን የማህበረሰብ የትግበራ እቅድን ማዘጋጀት፤
- የትግበራ እቅዱን መተግበር እና መከታተል፤
- አሳታፊ ቁጥጥር እና ክትትል፤

## 3.2 ባህሪያት እና መድሎዎች

በዋነኝነት ለሂደቱ ጥራት የዘዴዎቹ እና የመንገዶቹ አይነት ሳይሆን ዋነኛው ቁልፍ በባለሙያዎች እና የገጠር ነዋሪዎች መካከል ያለው ማህበራዊ ግንኙነት ነው፡፡ የዋና እቅድ ቡድኑ አባላት ቅን እና ፍላጎት ያላቸው መሆን እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ከዚህ በፊት የተለይዩ ዘዴዎችን በብዝበዛ እና ስለ አርብቶ አደር እውቀት እና አመለካከት በአግባቡ ሳጥጠና የአሳፊ የገጠር ግምገማን አላግባብ መጠቀም ተስተውሏል፡፡ በመሆኑም፣ ባህሪ እና አመለካከት አንድን ዘዴ በትክክል ከመጠቀም ይልቅ እጅግ ጠቃሚ ናቸው፡፡

ምስል 2: የአስተባሪዎች ሚና




| አመለካከት… | አመላካቾች |
| --- | --- |
| እርሶት ያስተዋውቁ… | እውነተኛ መሆን፣ ግልጽ፣ እንደ ግለሰብ መግብባት |
| ማድረግ ይችላሉ… | በሰዎች ችሎ መተማመን |
| የተማሩትን መተው… | ነገሮችን ሰለሚመለከቱበት አቅጣጫ በጥልቀት ያስቡ |
| ይጠይቋቸው… | ሰዎችን ሰለሁኔታቸው፣ ቅድሚያ ስለሚሰጡት ጉዳይ እና ምክር ይጠይቋቸው |
| አይፍጠኑ… | ትእግስት ይኑሮት፣ ግዜ ይውሰዱ |
| ቁጭ ብለው ያዳምጡ ይማሩ… | እርሶ ብቻ አይናግሩ |
| ያስተባብሩ… | የክፍል ትምህርት አያድርጉት፣ አይተቹ ወይም አያስተምሩ |
| ስህተትን ይቀበሉ… | ከማይሰራው ወይም ከሚበላሸው ይማሩ |
| ዱላውን ይስጡ… | ቾክ ወይም እስክርቢቶ ወይም ማንኛውም ጉልበት የሚሰጥ ነገር |
| ዝም በል… | ዝም ማለት እና የትእግስት ጸጥታ |

ምስል 3: ለአስተባባሪዎች አመለካከት (ከቻምበርስ የተወሰደ፣ 2001)

በሂደቱ ውስጥ የአስተባባሪዎች ተለዋዋጭነት፣ ስለራሳቸው ቦታ እና ተገገርነት በጥልቀት ማወቅ ጠቃሚ ሂደት ነው። ይህም በእራስ አስተሳሰብ ላይ (ሀሳብ፣ አመለከት፣ ግንዛቤ እና ቅድመ-ዝንባሌ) በጥልቀት ማንጸባረቅ መቻል ማለት ነው። አስትባባሪዎች ባህሪያቸው እና ሀሳባቸው የአርብቶ አደሮችን አመለካከት እና ቃላት ሊቀርጽ ወይም ሊያዛባ ስለሚችል ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል። በአሳታፊ የማህበረሰብ እቅድ ውስጥ፣ ከራሳቸው አመለካከት የተለየ ቢሆንም ለአካባቢው እውቀት እና አመለካከት ቦታ ሊተዉ እና የራሳቸውን ሀሳብ እና አተረጓጎም ከመጫን ሊቆጠቡ ይገባል። አሳታፊ የገጠር ግምገማ የተሻለ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ወደ አካባቢው ማህበረሰብ ማምጣት ማለት አይደለም። የቡድን ሂደትን ማመቻቸት ማለት ነው።

## 3.3 የዋና እቅድ ቡድኑ ሚና እና ተግባር

አሳታፊ የማህበረሰብ እቅድ አወጣጥ ወርክሾፕ በአብዛኛው ከ 3-5 ቀናት (በተከታታይ ወይም በተለያየ ግዜ) እንደ አላማው ሁኔታ ሊወስድ ይችላል። ባለ ብዙ ትምህርት የውጪ የእቅድ ቡድን (ለምሳሌ፣ የልማት ኤንጀት፣ የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ ባለሙያዎች፣ ወዘተ…) የአካባቢን ማህበረሰብ ስለሁኔታቸው እንዲመረምሩ እና የተለዩትን ችግሮች ለመፍታት የወደፊት እንቅስቃሴዎቻቸውን እንዲወስኑ ይረዷቸዋል። ዋና እቅድ ቡድን አስተባባሪን፣ ማስታወሻ ያዥ እና ቡድን መሪን ይጨምራል። አብዛኛው የአርብቶ አደር ህዝብ አማርኛ ስለማይችል አስተባባሪው እና ማስታወሻ ያዡ የአፋርን ቋንቋ በደንብ ማወቅ አለባቸው። የማስታወሻ ሰጪው እና አስተባባሪው የዕቅዱን ሂደት ማስተባበር እና ስኬታማ አፈፃፀም አጠቃላይ ኃላፊነት ላለው ቡድን መሪ ኃላፊነት አለባቸው።

የቡድን መሪው: ማቀናጀት እና ሀላፊነት

- ለድርጅታዊ እና ሎጅስቲክ ጉዳዮች እና ለአጠቃላይ አተገባበር ኃላፊነት ያለው
- ቡድኑን ለህብረተሰቡ ያስተዋውቃል እንዲሁም ከአከባቢው ባለስልጣናት ጋር ይገናኛል
- አሳታፊ ሁነቶችን ያስተባብራል
- ንዑስ ቡድኖቹ ችግር ካጋጠማቸው ይረዳል
- የንዑስ ቡድኖችን የማጠቃለያ እና የሰነድ ሂደት ያመቻቻል

አስተባባሪው ልከኝነት ፣ ተነሳሽነት ፣ ስሜታዊነት

- የአሳታፊ የገጠር ግምገማዎች ዘዴን ለተሳታፊዎች ያስተዋውቃል እና ሂደቱን ያመቻቻል፤
- በግለሰብ ተሳታፊዎች መካከል እንደ አመላካች ይሠራል-ሰዎችን ያበረታታል፣ ያነሳሳ፤
- ጸጥ ያሉ ሰዎችን/ሴቶችን ያዋህዳል፣ ሁሉም አስተያየታቸውን መግለጽ መቻላቸውን ያረጋግጣ፤
- ቡድኑ በርዕሱ ላይ እንደሚቆይ እርግጠኛ ነው ነገር ግን ተጨማሪ መረጃዎችን ለማስተናገድ ተለዋዋጭ ነው፤
- ስለ ውይይቱ ጥሩ ግንዛቤ መኖሩን ለማረጋገጥ ሰዎች የሚናገሩትን በቃል ይደግማል፤
- የጊዜ አያያዝን ይቆጣጠራል፤

ማስታወሻ-ያዡ-ዝግጅት ፣ ሰነድ ፣ ምልከታ[2]

- አስፈላጊ ቁሳቁስ መገኘቱን ማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት
- የሂደቱን ከበስተጀርባ ይመለከታል እንዲሁም እንደ ቁልፍ መግለጫዎች ፣ ግጭቶች ፣ ከባቢ አየር ፣ የአካል ቋንቋ ያሉ አስፈላጊ መረጃዎችን ይጽፋል (ማስታወሻ-ሰጭዎችን ለመርዳት ፎርማቶች በአሳታፊ የመስክ መመሪያ ተዘጋጅተዋል)
- ማን እየተናገረ ያለው ማስታወሻዎች-አንዳንድ ሰዎች ሂደቱን ይቆጣጠራሉን? ሴቶች ይናገራሉ?
- የተሳታፊዎች ምስላዊ ሰነዶች ከመሬት መታየታቸውን ያረጋግጣል፤
- ቅጅው ከመጀመሪያው ጋር እንደሚመሳሰል ያረጋግጣል ፣ በዝግጅቱ ላይ የተሳተፉ ሰዎች አፈ ታሪክ ፣ ቀን ፣ ቦታ እና ስሞች አሉት።

2 ይህንን ተግባር በሁለት ሰዎች መካፈል ይመከራል፤ በእይታ ውስጥ የሌሉ ውጤቶችን እና ስምምነት የተደረሰባቸውን ጉዳዮች ማስታወሻ መያዝ እና መሰነድ እና ሌላ ሰው ደግሞ ሂደቱን የሚከታተል እና ማስታወሻ የሚይዝ

## 3.4 የአሰራር መሳሪያ ሳጥን

### 3.4.1 በከፊል ቅርጽ ያለው እና የትኩረት ቡድን ቃለ-መጠይቅ

ሁሉም የአሳታፊ የገጠር ግምገማ መሳሪያዎች ኳሊታቲቭ ቃለመጠይቅ ዘዴ ዋነኛው ክህሎት ሲሆን ብዙ ግዜ ስለሚወስድ እና ልምድ ስለሚጠይቅ አስቸጋሪ ነው። አስተባባሪዎች የተለየ ምልከታ አድርገው ወይም ሳያደርጉ የአካባቢውን ሁኔታ እንዲረዱ እራስን በአግባቡ ማወቅ (ቦታን ማወቅ)፣ በጥሞና ማዳመጥ እና ጥንቃቄ የተሞላበት ምልከታን የመሰሉ የቃለ-ምልልስ ክህሎቶች አስፈላጊ ናቸው። በዚህ መመሪያ የተገለጹት ጠንካራ የኳሊታቲቭ ቃለ-ምልልስ ክህሎቶች ዋጋ ትልቅ ነው።

የቃለ መጠይቅ መመሪያ (ከፕሪቲ እና ሌሎችም የተወሰደ 1988)

1. የማረጋገጫ ዝርዝር ወይም የቃለ-መጠይቅ መመሪያ ይኑሮት
2. ለተሳታፊዎች በሙሉ አክብሮት ማሳየት እና ለስሜታቸው መጨነቅ
3. ተሳትፎን እና ውይይትን ለማሳደግ የእይታ ዘዴዎችን ይጠቀሙ
4. ማዳመጥ እና መማር
5. ክፍት ጥያቄዎችን መጠየቅ ለምሳሌ ማን? ምን? ለምን? እንዴት? የት? መቼ?
6. የድጋሚ ጥያቄ በጥንቃቄ ማቅረብ
7. መልሶችን በእውነታ፣ አመለካከት/ አስተሳሰብ፣ ሀሜት መለየት፤
8. በሶስትዮሽ ሂደት ማጣተራ
9. መልሶችን እና መረጃዎችን በተቻለ መጠን በተሟላ መንገድ መመዝገብ

የኳሊታቲቭ ቃለ-መጠይቅ (በከፊል የተደራጀ፣ የትኩረት ቡድን ቃለመጠይቅ/ውይይት፣ የትረካ ቃለ-መጠይቅ) ዋና ባህሪያት ግልጽነት እና ተለዋዋጭነት ናቸው። ቃለ-መጠይቅ ቀለል ያለ ንግግር ሊመስል የሚችለው የመማር ፍላጎት ያላቸው እና የተለያዩ አመለካከቶችን መረዳት ለሚፈልጉ፣ የቃለመይጠቅ ሰጪውን አመለካከት መረዳት የሚፈልጉ ቃለመይጠቅ አድራጊዎች ብዙ ጣልቃ ሳይገቡ ቃለመጠይቅ ሲያደርጉ ነው። የተለያዩ መላሾች ምላሽ ተነጻጻሪ እንዲሆን የጥያቄ መመሪያ አስቀድሞ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ነገር ግን የጥያቄዎቹ ቅደም ተከተል በቃለ-መይጠቁ ወቅት የሚወሰን ነው። ከዚህ ቀምደ በተሰጡ መልሶች መሰረት በእቅድ አወጣጥ ወቅት የማረጋገጫ ዝርዝር ሊዘጋጅ ይችላል።

በእይታ የታገዘ ክፍለግዜ መጨረሻ ክፍት ጥያቄዎችን መጠየቅ ዋነኛ ጠቀሜታው፤

1. በእይታ የታገዘ ክፍለ ግዜ ወቅት ሊኖር የሚችለውን አለመግባባት ለመፍታት ይጠቅማል፤
2. በመልመጃዎቹ ወቅት ዝም ያሉትን ሰዎች አመለካከት ለማየት
3. በቡድን መለመጃዎቹ ወቅት ያልተነሱ ሀሳቦችን ለማንሳት፤
4. በእይታ የታገዙ መልመጃዎችን በተመለከተ ቃለ-መይጠቅ ማድረግ፤

### 3.4.2 የሀብት ካርታ

የሀብት ካርታ የበለጠ ውይይት ስለሚያነሳሳ ለመጀመር ጥሩ ዘዴ ነው። የአርብቶ አደር ሀብቶች ወቅትን መሰረት ያደረጉ ስለሆኑ  ካርታውን በወቅት ከፋፍሎ ማዘጋጀት ያስፈልጋል።


አላማ:

የሀብት ካርታን ማዘጋጀት የሀብትን አይነት፣ ተያያዥ ችግሮችን እና ተግባራትን ለመለየት ይረዳል። ካርታው የአካባቢው ማህበረሰብ ሚና የሚጫወትለት ሀብት (የትኛው፣ የት፣ እንትዴ ጥቅም ላይ ይውላል እና ሌሎች ችግሮች) ላይ ያለውን አመለካከት ለመረዳት ይረዳል። ቦታው በትክክል መቀመጥ አለመቀመጡ ከግምት አይገባም። በአካባቢው ማህበረብሰ ዘንድ ያሉት ሁሉም ሀብቶች ጥቅም ላይ የሚውሉ ላይሆኑ ይችላሉ። በአርብቶ አደር አካባቢዎች፣ የከብቶች እንቅስቃሴን[3] እና የሀብቶችን ወቅት ተኮርነት ካርታው ላይ ማሳረፍ አስፈላጊ ነው።

3 ተሳታፊዎች የተለያየ የእንቅስቃሴ ካርታ እንዲሰሩ በመጠየቅ ከብቶች በደህና አመት እና በድርቅ ወቅት እንቅስቃሴያቸውን እንዲያሳዩ ማድረግ። እንቅስቃሴዎቹ በከብት እና በግመል መካከል ያለውን ልዩነት ሊያሳዩ ይገባል። ቁልፍ የመሬት አቀማመጦች መጀመሪያ ሊሳሉ ይገባል።

ሂደት:

- ተሳታፊዎች የሚመቸውን መርጠው እንዲወስኑ ማድረግ (ቦታ፣ ጥላ፣ በቀላሉ የሚገኝ).
- ተሳታፊዎች ጠቃሚ ሀብቶችን እንዲለዩ ይጠይቋቸው (ለምሳሌ የግጦሽ አካባቢ፣ የእርሻ አካባቢ፣ ጫካ፣ መስፈሪያዎች፣ ጉድጓድ፣ ወንዝ)፤ የትኞቹ በአካባቢው የሚገኙ ሀብቶች ናቸው ለእርሶ በጣም ጠቃሚ የሆኑት? የካርታ አዘገጃጀቱን ለማስጀመር አስተባባሪው የመጀመሪያውን ይዘት ያስቀምጣል (ለምሳሌ፤ ሰፈራን የሚያመላክት ድንጋይ)።
- በካርታው ላይ ከሀብት ጋር የተያያዙ ችግሮችን እንዲጠቁሙ ተሳታፊችዎን ይጠቋቸው (ለምሳሌ ደለል፣ የተሸረሸሩ የግጦሽ አካባቢዎች፣ የግጭት አካባቢዎች ወዘተ)። መሳላቸውን እስካላቆሙ ድረስ ጣልቃ መግባት አይገባም።
- ካርታው ሲጠናቀቅ፣ አስተባባሪዎች ተሳታፊዎች እንዲገልጹት ሊጠይቋቸው ይገባል። ይህም ስለ ሀብቶች እና የመሬት አጠቃቀም የቡድን ውይይት ሊያስነሳ ይገልባል። አስተባባሪዎች መመሪያ ጥያቄዎችን ሊያዘጋጁ ይገባል።
- የካርታው መልመጃ በተሳታፊዎች ፎቶ ተነስቶ ወደ ወረቀት ወይም ጂአይኤስ ሊቀየር ይገባል። በተሳታፊችዎ የተዘጋጀው ካርታ ቁልፍ የካርታው አካል መሆን አለበት። ሰዎች መጻፍ የማይችሉ ከሆነ በአስተባባሪው ሊከናወን ይገባል።




ምስል 4: የሀብት ካርታ፣ ሜን፣ ለአስ፣ ገዋኔ ወረዳዎች፣ ኢትዮጵያ 1998 (የራሳቸው ሀብት)

ተሳታፊዎች:

የራሳቸውን እውቀት ያቀላልሉ ትልልቅ የተቀላቀሉ ቡድኖች ወይም ስለ ሀብት ጥቅም የተለያየ አመለካከት ሊኖራቸው የሚችል ቡድኖች ለምሳሌ ወንዶች/ሴቶች፣ አርብቶ አደሮች እና ከፊል አርብቶ አደሮች።

1-2 ሰዓታት

የሚፈለጉ ቁሳቁሶች:

እስክርቢቶዎች ላለመደ ሰው ካርታ መሳል ከባድ ሊሆን ይችላል። የተሻለው አማራጭ የተፈጥሮ ሀብቶችን ለምሳሌ ዱላ፣ ድንጋይ፣ ቅጠል ወዘተ... መጠቀም ነው። የድሮን ምስሎች ወይም ኦርቶ ፎቶዎች ለውይይት ወይም ካርታ ለመሳል ለመነሻነት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ።

### 3.4.3 ወቅት ተኮር ምስል

አላማ:

ወቅት ተኮር የግዜ መቁጠሪያ የርእሶቹን ወቅታዊ ለውጥ ለማትየ ይጠቅማል። በተፈጥሮ የወቅት መፈራረቅ፣ የምግብ ዋስትና፣ እንቅስቃሴን/የማህበረሰብ አካል በቦታው አለመኖር፣ የቀንድ ከብት ዋጋ፣ ገቢ፣ በሽታ፣ ጾታን መሰረት ያደረገ የስራ ጫና፣ ወዘተ….. ያላቸውን የእርስ በእርስ ግንኙነት ለማሳየት ይጠቅማል። ያጋጠሙ ችግሮችን እና እድሎችን በግዜ ከፍሎ ያያል። የትኞቹ ከግምት እንደሚገቡ የሚወስነው የእቅድ ሂደቱ አላማ ነው።

ሂደት፤

1. ሰፊ ክፍት ቦታ ለቡድኑ መፈለግ፤
2. ተሳታፊዎቹን ማትሪክስ እንዲስሉ ይጠይቋቸው (በመሬት ወይም በወረቀት ላይ)፣ በአግዳሚው ላይ ወሮችን ይዘርዝሩ
3. የግዜ መቁጠሪያውን የዝናብ ሁኔታን በመጠየቅ መጀመር ቀላል ነው። ለዝናብ የሚሆን ምልክት ምረጡ እና ተሳታፊዎች ዝናብን ለማብራራት በሚጠቀሙበት አካባቢ ይሳሉት። የዝናብ መጠንን ለመወከል የቡድኑ አባላትን በእያንዳንዱ ወር ላይ ድንጋዩን እንዲያስቀምጡ ይጠይቋቸው። (ብዙ ድንጋይ ማለት ብዙ ዝናብ ማለት ነው)።
4. ወደ ሚቀጥለው ቡድን በመሄድ በየትኛው ወቅት ምግብ እንደሚያጥር ይጠይቋቸው። ለምን እንደሚያጥር ተወያዩ፣ ለሰዎች የሚሰጡ የተለያዩ የምግብ እርዳታዎችን ተወያዩባቸው። ይህም መረጃ በግዜ መቁጠሪያው ላይ መኖሩን ያረጋግጡ።
5. በእደዚህ አይነት ሁኔታ ሁሉንም ርእሶች ይሸፍኑ። ጥያቄዎችን በመየቅ ያስተባብሩ፤ የትኛው ወቅት ነው ለወንዶች እና ለሴቶች ተገቢ ተጨማሪ እንቅስቃሴዎችን ለማከናውን አግብባ የሆነው? ምን አይነት የግዜ እጥረቶች እና በምን ምክንያት ይከሰታሉ? ሌሎች ርእሶች የሚከተሉትን ይጨምራሉ:
    - ገቢ (በጥሬ እና በአይነት) ለሴቶች ወይም ለወንዶች
    - ወጪ ለወንዶች እና ለሴቶች
    - ለሰው መጠቀሚያ የሚሆን የውሃ አቅርቦት
    - የከብት መኖ
    - የብድር አገልግሎት መኖር
    - የእርሻ ስራ ጫና ለሴቶች እና ለወንዶች
    - ከግብርና ውጪ ያሉ ስራዎች ጫና ለወንዶች እና ለሴቶች

እንደ ተሳታፊዎቹ ፍላጎት ተጨማሪ ጉዳዮች ሊጨመሩ ይችላሉ፤

6. የግዜ መቁጠሪያው ሲጠናቀቅ፣ ቡድኑን የትኛው ትስስር እንደሚታያቸው ይጠይቋቸው። ቡድኖቹ በቀን መቁጠሪያው ላይ የሚመለከቱትን እንዲወያዩበት ያበረታቷቸው።
7. የሚኖሮት የወቅት የግዜ መቁጠሪያ በካርታው ላይ ጥቅም ላይ የዋሉ የተለያዩ ምልክቶችን እና ቁሳቁሶችን ያካተተ እንደሆነ ያረጋግጡ።

የሚፈለጉ ቁሳቁሶች፤

በመሬት ላይ የተሳለ ከሆነ፤ ምልክቶቹን ለማድረግ ጥቅም ላይ የዋሉ ድንጋዮች፣ ዱላዎች፣ እና ሌሎች ቁሳቁሶችን እንዲሁም ወቅትን ያማከለ የግዜ መቁጠሪያ ለማዘጋጀት ትልልቅ ሰነዶችን ማዘጋጀት

በወረቀት ላይ የተሳለ፤ ትልልቅ ወረቀቶች፣ እስራስ እና የተለያየ ቀለም ያላቸው ማርከሮች

2 ሰዓት

የሚከተለው ምስል 6 በአፋር ከሚኖሩ ያልተማሩ አርብቶ አደሮች ጋር የተሰራ ምስል ማሳያ ነው:: ለሁሉም ለመረዳት ቀላል የሆኑ ምልክቶች ጥቅም ላይ ውለዋል:: ቁልፉ የምልክቶቹን ትርጉም ይገልጻል::

| | ዝናብ | የውሃ ጥራት | ወባ | ግጭት | የወተት ምርት | የገቢ መኖር | የከብት ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ግላል | | ☹ | ከፍተኛ | ☼ ☼ | | ○ | ዝቅተኛ |
| ዳዳ | ☁ | ☹ | ከፍተኛ | ☼ | መካከለኛ | ○ ○ | መካከለኛ |
| ሶጉም | ☁ ☁ ☁ | ☺ | ዝቅተኛ | ☼ ☼ ☼ | ከፍተኛ | ○ ○ ○ | ጥሩ |
| ሀጋይ | | ☹ | ዝቅተኛ | ☼ | ከፍተኛ | ○ ○ ○ | ጥሩ |
| ካርማ | ☁ ☁ ☁ | ☺ | ዝቅተኛ | ☼ ☼ ☼ | ከፍተኛ | ○ ○ ○ | ጥሩ |
| ቁልፍ | | ☺ ጥሩ<br>☹ መጥፎ | | | | | |

ምስል 5: ወቅትን መሰረት ያደረገ የግዜ መቁጠሪያ፣ ለአስ፣ ገዋኔ ወረዳ፣ 1998 (የግል ምንጭ)

### 3.4.4 የባለድርሻ አካላት ምርመራ: ቬን ዲያግራም

አላማ:

ቬን ዲያግራሞች ተቋማዊ እና ማህበራዊ ሁኔትዎችን እና አቅሞችን ጠቅላላ ለመለየት የሚያገለግል ቀላል እና ጠቃሚ መንገድ ነው:: ተሳታፊዎች ዋና ጉዳዮችን በሚመለከት ከማህበረሰቡ ውስጥ እና ውጪ የተቋማትን ጥቅም እና ውጤታማነት ለማተየ የሚረዳ ነው:: ተቋማዊ ግንኙነት እና ችግሮች በውይይቱ ወቅት ግልጽ ሆነዋል:: ደካማ ወይም ግንኙነት የሌላቸው እንዲሁም ትብብር እና ግጭት ያለባቸው ይለያሉ:: ይህ ዘዴ በአሁን ወቅት ባሉ ተቋማዊ አቅሞች፣ የትኞቹ ሰዎች የትኞቹን ተቋማት ማግኘት እንደሚችሉ እና የትኞቹ ተቋማት የልማት ሂደትን እንደሚደግፉ ለመለየት ይጠቅማል:: ቬን ዲያግራም ግጭቶችን ለመፍታት የትኞቹ ተቋማት የተሻለ ተቋማቂ ሁኔታ እንዳላቸው ለመለየት፣ ተቋማዊ ክፍተቱን ለመዝጋት እና ትስስሮችን ለማበረታታት ይረዳል::

ሂደት:

- ለተሳታፊዎች የቬን ዲያግራምን አላማ ማብራራት፤
- ሁሉንም ተቋማት እንዲለዩ መጠየቅ (ባህላዊ፣ መንግስታዊ፣ የግል ወዘተ....) ወይም ለጉዳዩ ጠቀሜታ ያላቸው ግለሰቦች ለምሳሌ፤- የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ:: ይህም ውጫዊ እና ውስጣዊ ተቋማትን እና ግለሰቦችን ይመለከታል::
- ተሳታፊዎች መተዳደሪያቸውን በተመለከተ ተጽእኖ የሚያመጣ፣ አንጻራዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ተቋማትን እንዲለዩ ይጠይቋቸው:: የተለያየ መጠን ያላቸው ክቦች የጠቀሜታቸውን ልዩነት ይጠቁልማ (ትልቅ፤ በጣም ጠቃሚ፣ መካከለኛ: አነስተኛ ጠቀሜታ ያለው፣ ትንሽ: ጥቅም የሌለው)::
- ማህበረሰቡ እራሱን በትልቅ ክብ መሀከል ላይ ይወክል:: ጠቃሚ ስለ ሆኑ ባህላዊ ተቋማት እና ግለሰቦች ይጠይቁ እና እነዚህንም በማህበረሰብ በመክበብ ያስቀምጡ::
- ሌሎቹንም ተቋማት በማህበረሰቡ አካባቢ እንዲያስቀምጧቸው ይጠይቋቸው:: በክቦቹ መካከል ያለው ርቀት የግንኙነታቸውን መጠን ያሳያል:: ግጭት ወይም የግንኙነት አለመኖርን ሊያመለክትም ይችላል::


ተሳታፊዎች:

8-12, የተቀላቀሉ ቡድኖች፣ በማህበረሰቡ ውስጥ አመለካከት ሊለያይ ስለሚችል በተለይዩ ቡድኖች ውስጥ መልመጃውን መስራት አስፈላጊ ነው::

1-2 ሰዓታት

የሚፈለጉ ቁሳቁሶች:

ትልቅ ወረቀት፣ ማርከሮች፣ የተፈጥሮ ቁሳቁስም ይቻላል




ምስል 6: ቬን ዲያግራም፣ ማርቀቅft

ከላይ ባለው ምስል ውስጥ ያሉት ክቦቹ መካከል ያለው ርቀት ከወረዳው የውሃ ቢሮ ጋር ግጭት ወይም ችግር እንዳለ ያሳያል፣ ይህም የክቡን ትልቅነት ከግምት ውስጥ በማስገባት የተቋሙን የውሳኔ መስጠት ሀይል ጠቃሚነት ያመላክታል። ሌላው ዋነኛ ውጤት በፒዲኦ እና በወረዳው ትምህርት ቢሮ መካከል ያለውን ጥሩ ግንኙነት ያሳያል።


## 3.4.5 ውጤት እና ደረጃ፤ ችግሮችን እና መፍትሄዎችን ቅድሚያ መስጠት

እነዚህ ዘዴዎች ቅድሚያ መስጠት እና ውሳኔ አሰጣጥ ጋር የተገናኙ ሂደቶች የተመለከቱ ጉዳዮችን ማለትም ችግሮች፣ አቅሞች፣ መፍትሄዎች፣ ፍላጎቶች ወዘተ... እና የማህበረሰብ እቅድን በተመለከተ ጠቃሚ ናቸው። ጠቃሚዎቹ መልመጃዎች ከስር የተገለጹት ናቸው፤ ቀላል ደረጃ አሰጣጥ፣ ፍልጎትን ደረጃ መስጠት እና ማትሪክስ ውጤት ናቸው። ደረጃ እና ውጤት አስተሳሰቦች እቅግ የተለያዩ ወይም እጅግ አንድ አይነት እንዴት እንደሆነ ያሳያል። ለተሳታፊዎች እጅግ ጠቃሚው ክፍል የመጨረሻው ማትሪክስ ብቻ ሳይሆን፣ በማትሪክሱ ዝግጅት ወቅት የሚኖረው የእውቀት እና ልምድ ልውውጥ እንደሆነ ማስታወስ ያስፈልጋል። ለተሳታፊዎች የቃለመጠይቅ ማትሪክስ የሚለው ቃል ለዚህ መልመጃ በብዛት ጥቅም ላይ የሚውል እንዳልሆነ ማስታወስ ያስፈልጋል።

ቀላል ደረጃ አወጣጥ/ የምጥጥን መሙላት

አላማ:

ይህ ዘዴ አሉ ተብለው በሚታሰቡ ችግሮች፣ ፍላጎቶች፣ የፕሮጀክት ሀሳቦች እና ርእዮች ላይ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ይረዳል። የተለያዩ ማህበራዊ ቡድኖች የተለያዩ ቅድሚያ የሚሰጧቸው ጉዳዮች እንዳሉ ማየት ይቻላል። የዛፍ ዝርያዎችን፣ የግጦሽ ሳርን፣ የእርሻ መሬትን ተነጻጻሪ ዋጋ ለመለየት ይረዳል። ከተዘረዘሩት ውስጥ የትኞቹ ጠቃሚ፣ አስፈላጊ እና ምቹ ናቸው? በዚህ ምሳሌ ተሳታፊዎች መጀመሪያ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባቸውን ጉዳዮች ከተወያዩ በኋላ ሁሉም 10 ድንጋዩችን በየርእሱ አሰባብረዋል፤ ብዙ ድንጋዮች ማለት ችግሩ የጠነከረ ነው ማለት ነው። በውይይቱ የተገለጸው በሽታ ማለት ብዙ ግዜ ወባ ወይም ውሃ ወለድ በሽታ ሲሆን፣ የውሃ ችግር ማለት የውሃ መበከል ማለት ነው። በተለይም ደረጃ አሰጣጡ ግልጽ ካሆነ አስፈላጊ ነው፣ ማትሪክሱን ቃለ-መይጠቅ ማድረግ። ውይይቱ ስለተገኙት ችግሮች ምክንያት ማሳወቅ ችሏል ለምሳሌ፤ የግጦሽ ማጣት በፕሮሶፒስ ጁሊፍሎራ እና በኢሳ እና ሶማሌ ግጭት ምክንያት የተከሰተ ነው።




ምስል 7 የደረጃ አሰጣጥ ችግር፣ ሌአስ፣ ገዋኔ ወረዳ፣ ኢትዮጵያ 1998 (የግል ምንጭ)

### የፍላጎት ደረጃ

አላማ:

ከቀልሉ ደረጃ አሰጣጥ አንጻር የፍላጎት ደረጃ አሰጣጥ ፍላጎትን በተመለከተ የአካባቢው ውሳኔ አሰጣጥ ምን እንደሚመስል ያሳያል። እያንዳንዱ ሁኔታ ከከፍተኛ እስከ ዝቅተኛ ደረጃ እስኪኖረው ድረስ፤ በቀጥታ አንዱ ከሌላው ጋር ይነጻጸራል። በአግባቡ ሊመዘገብ የሚገባው ምክንያት በተሳታፊዎች (በመልመጃው ወቅት እና ከዛ በኋላ) መካከል ውሳኔያቸውን አስመልክቶ የተደረገ ውይይት ነው። አስተባባሪዎቹ ይህ ሂደት ሊያስተባብሩ እና ሰዎች የተወሰኑ ርእሶችን ብቻ ለምን እንደሚመርጡ መጠየቅ እና ከሌሎች ውጤቶች ጋር ሊያነጻጽሩ (ማትሪክሱን ሊያዩ) ይገባል።

### ሂደት

- የመልመጃውን አላማ እና ቁልፍ ጥያቄዎች ያብራሩ፡
- ተሳታፊዎች ቅድሚያ እንዲሰጧቸው የሚፈልጓቸው ስድስት ጉዳዮች ብቻ እንዲመርጡ ይጠይቋቸው፤
- ሰዎች ሁለት ነገሮችን እንዲያነጻጽሩ እና የትኛው ችግር እንደሚበልጥ እና በቅድሚያ እንዲፈታ እንደሚፈለጉ ይጠይቋቸው። ሰዎች የውሳኔያቸውን ምክንያት ማብራራት አለባቸው!
- ማስታወሻ ያገፑ ውይይቱን ሊሰንደው ይገባል።
- እያንዳንዱ ችግር ስንት ግዜ እንደተፈጠረ ይቁጠሩ፣ ያስቆጠረውን ይቁጠሩ እና ደረጃ ያውጡ። በመጨረሻም ያወዳድሩ እና ተሳታፊዎችን የደረጃ አወጣጡ አስተሳሰባቸውን እንደሚወክል ይጠይቋቸው።

| ችግር | ድርቅ | የእንስሳት በሽታ | የሰው በሽታ | የውሃ እጥረት | የመሬት መሸርሸር |
|---|---|---|---|---|---|
| ድርቅ | | ድርቅ | ድርቅ | ድርቅ | ድርቅ |
| የእንስሳት በሽታ | | | የሰው በሽታ | የውሃ እጥረት | የመሬት መሸርሸር |
| የሰው በሽታ | | | | የሰው በሽታ | የሰው በሽታ |
| የውሃ እጥረት | | | | | የውሃ እጥረት |
| የመሬት መሸርሸር | | | | | |

| ችግር | ድግግሞሽ | ደረጃ |
|---|---|---|
| ድርቅ | 4 | 1 |
| የእንስሳት በሽታ | 0 | 5 |
| የሰው በሽታ | 3 | 2 |
| የውሃ እጥረት | 2 | 3 |
| የመሬት መሸርሸር | 1 | 4 |

ምስል 8: በጥንድ ችግሮችን ማነጻጸር (ከአፋር አሳታፊ የገጠር ግምገማ ስልጠና የተወሰደ, 2013))

የማትሪክስ ውጤት እና ደረጃ: አማራጮችን መመርመር

አላማ:

የማትሪክስ ደረጃ አወጣጥ የተለያዩ አማራጮች በመጠቀን የሚሰራ ደረጃ አወጣጥ ነው:: ይህ ውይይት ሰዎች ከተለያዩ አማራጮች መካከል መምረጥ ሲኖርባቸው አገልግሎት ላይ ይውላል:: የሚመረጡ ተግባራትን፣ ሀብቶችን ወይም አይነቶች (አዝእርት፣ የቀንድ ከብቶች) እና የነዚህን ምርጫዎች ምክንያት ለመለየት ጠቃሚ መሳሪያ ነው::

ለምሳሌ፣ የተለያዩ ዛፎች ዘሮች የተለያዩ መስፈርቶችን መሰረት ማድረግ ለምሳሌ የማገዶ እንጨት፣ ለግንባታ፣ የፍራፍሬ ዛፍ፣ የህክምና ዛፍ፣ የአፈር መሻሻል ዛፍ ወዘተ  መስፈርት መሰረት ይገመገማሉ:: ተሳታፊዎች የተለያዩ ዘሮችን ጠቃሚነት መገምገም ሲፈልጉ ዋና ሚናን የሚጫወቱ ዘሮችን ይመርጣሉ::  ይህ መረጃ የልማት ኤጀንሲዎች እና ድርጅቶች ስትራቴጂክ እቅዶችን ሲነድፉ ያስፈልጋቸዋል::

ሂደት:

- የመልመጃውን አላማ እና ቁልፍ ጥያቄዎች ያብራሩ፤
- ማነጻጸር ስለሚፈልጓቸው ሁለት ነገሮች (የመሬት አማራጭ፣ የዘር አይነቶች፣ የግጦሽ ምንጭ፣ የእንስሳ ዘር፣ ችግሮች፣ መፍትሄዎች ወዘተ.....) ማውራት ይጀምሩ:: ሁሉም ተሳታፊዎች ሁሉንም አማራጮች በተመለከተ ተመሳሳይ አረዳድ እንዲኖራቸው ያድርጉ::
- ተሳታፊዎችን የትኛውን መስፈርት መውሰድ እንደሚገባ ይጠይቋቸው:: የትኛው መወሰድ እንዳለበት ሀሳብ ሊሰጡ ይችላሉ፤ ነገር ግን ተሳታፊዎች የራሳቸውን ሀሳብ እንዲያፍልቁ ያበረታቷቸው:: ምርጫቸውን አስቀድመው ከወሰኑ፣ መስፈርቱንም አስቀድመው ይወስናሉ:: ሰዎች በአንድ መስፈርት ከተስማሙ፣ የጋራ ስምምነት የደረሰበትን ምልክት በማስቀመጥ በካርድ ላይ ሊጻፍ ይገባል::
- ከተሳታፊዎች ጋር ክፍልፋዮች በማዘጋጀት ካርዶቹን በማትሪክስ ውስጥ ማስቀመጥ ያስፈልጋል (አማራጭ እቃዎች በረድፍ ከላይ፤ የመስፈርት ዝርዝር በአምድ ከግራ በኩል)
- የመገምገሚያ መንገዶችን ያብራሩ (ለምሳሌ: 5: ከፍተኛ ደረጃ፣ 1: ዝቅተኛ ደረጃ) እና እያንዳንዱን አላማ እና መስፈርት ያብራሩ:: ተሳታፊዎች ሂደቱን እንዲመሩት ይፍቀዱላቸው፤ መስፈርቶችን በደንብ ከተረዷቸው ውጤት መስጠቱን እራሳቸው ይተገብሩታል:: ግምገማቸው ላይ ተጽእኖ ከማሳደር ይቆጠቡ::
- ማስታወሻ ወሳጁ የተለይዩ ማብራሪያዎችን፣ ውይይቶችን እና ውጤቶችን ይመዘግባል::
- በመጨረሻም፣ ውጤቱን በአንድ ላይ በመደመር ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ነገሮች ላይ አጠቃላይ ያለውን ውጤት ይወያዩበት::

| መስፈርት/ ዘር | ሙፓኔ | ሙፎንዶ | ሙፓንዳ | ሙሱሱ | ምፓዋዛ |
|---|---|---|---|---|---|
| የቅጠሎች ቶሎ መብቀል | 7 | 4 | 5 | 2 | 2 |
| ለምግብነት የሚውሉ ቅጠሎች | 1 | 0 | 0 | 19 | 0 |
| ጥሩ ጣእም/ጨዋማ | 7 | 4 | 5 | 2 | 2 |
| ከፍተኛ የውሃ መጠን | 0 | 0 | 13 | 0 | 7 |
| ጠቅላላ ደረጃ | 1 | 4 | 3 | 2 | 5 |

ምስል 9: ማትሪክስ ደረጃ፣ ከዚምባብዌ    የተወሰደ ምሳሌ (ስኩንስ 1987)

በምስል 9 አርሶ አደሮች የተለያዩ ዘሮችን ለማሰስ ምቹ መሆናቸውን መሰረት አድርገው ይመርጧቸዋል:: ለእያንዳንዱ መስፈረት 20 ድንጋዮች ለገበሬዎች ተከፋፍሏል:: በአጠቃላይ ያለው ደረጃ ከውጤት አሰጣጡ ጋር ላይዛመድ ይችላል፤ ይህም በተለያዩ ምክንያቶች ያለውን መለኪያ ልዩነት ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይችላል::

### 3.4.6 ችግር/ የአላማ ዛፍ: አገናኝ ምክንያቶችን መለየት


የችግር ዛፍን መሳል ማሰላሰል እና የደረጃ መልመጃን ለማከናወን እና ችግሮችን ለመለትየ እና ቅደም ተከተል ለማስያዝ ይረዳል፡፡ ዛፉ ከሚከተትሉ በአንዱ ችግሮች ላይ ያተኩራል፤ ይህም ብዙ ግዜ በአካብቢው ሰዎች ከፍተኛ ቦታ የተሰጠው ነው፡፡ የዛፉ ግንድ ማህበረሰቡ ከፍተኛ ነው ብሎ የሚያስበውን ችግር ይወክላል፡፡ የዛፉ ስሮች የችግሩን ምንጮች እና ቅርንጫፎቹ ደግሞ ጉዳቶቹን ያመለክታሉ፡፡

አላማ:

የችግር ዛፍ ወይም የአላማ ዛፍ ተሳታፊዎች ዋና ዋና ችግሮችን እንዲለዩ እና ዋና ችግሮችን ምክንያት እና ውጤት እንዲሁም መፍትሄዎችን እንዲያውቁ ይረዳል፡፡ ይህ ዘዴ የችግር ምርምርን ከመፍትሄ ስትራቴጂ ዝግጅት ጋር የሚያገናኝ ነው፡፡

ሂደቶች:

1. ዋናው ችግር በተሳታፊዎች መለየት አለበት (ይህም አስቀድሞ የተሰራው የደረጃ አሰጣጥ ውጤትን ይገልጻል) እና በወረቀት፣ በግርግዳ ወይም በመሬት ላይ እንዲታይ ማስቀመጠት፡፡
2. ተሳታፊዎች በችግሮቹ ምክንያት እና ጉዳት ላይ ሀሳብ እንዲሰጡ እና ሁሉንም አረፍተ ነገሮች በአሉታዊ እንዲጽፏቸው ያድርጉ፡፡ የችግሩ ምክንያቶች እና ጉዳቶች በግልጽ እና በአመክንዮ መቀመጣቸውን ለማረጋገጥ ቅደም ተከተል መያዙን ማረጋገጥ፡፡ በተሳታፊዎች መካከል ስምምነት መኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ለአንድ ውጤት ከአንድ በላይ ምክንያቶች ካሉ፣ ጎን ለጎን ማድረግ ይቻላል፡፡ ላልተማሩ ቡድኖች፣ ተሳታፊዎችን ለእያንዳንዱ ምክንያት እና ውጤት አንድ ምልክት እንዲያደርጉ ጠይቋቸው እንዲሁም ተሳታፊዎቹ ምልክቶቹን እንዲረዱ በተደጋጋሚ ምልክቶቹን ያንብቧቸው፡፡
3. ወደ ስትቲቴጂ ውይይቱ ለመሄድ የችግር ዛፉ ወደ አላማ ዛፍ መቀየር አለበት፡፡ የአላማ ዛፍ የሚሰራው የችግር ዛፉ የተፈጠረባቸውን አሉታዊ አረፍተ ነገሮች ወደ አወንታዊ አረፍተ ነገሮች በመቀየር ነው፡፡ ለምሳሌ፦ “የእውቀት ማጠር”ን የመሰለ ምክንያት፣ “ተጨማሪ እውቀት” የመሰለ መፍትሄ ይሆናል ማለት ነው፡፡ የአላማ ዛፍ በአላማዎች መካከል ያለውን የምክንያት እና ውጤት ግንኙነት ያሳያል፡፡
4. የመጨረሻው ደረጃ ለመፍትሄ የሚሆን ስትራቴጂ መምረጥ ነው፡፡ ሁሉንም ችግሮች ለመፍታት የሚቻል ላይሆን ይችላል- ስለሆነም ያሉትን ሀብቶች በመመርኮዝ ተሳታፊዎች ሊወስኑ ይገባል፡፡ ይህ ተገቢውን ስትራቴጂ ለመቀየስ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ የተለያዩ ፍላጎቶችን ለማሟላት እና ለጾታ ተኮር አቅሞች እና ችግሮች የተለየ ትኩረት የሚሰጥ፣ ጥሩ ማስተባበር የሚጠይቅ እጅግ በጣም አስቸጋሪ ደረጃ ነው፡፡ የሚነሱ የተለመዱ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፤ የተነሱትን ሁሉንም ችግሮች መፍታት ወይስ የተወሰኑትን መምረጥ ይቻላል? የትኞቹ መፍትሄዎች ተፈላጊውን ውጤት ያመጣሉ? የተሻለ ጥቅም የሚያመጣው የትኛው ነው? እነዚህ መፍትሄዎች የረጅም ግዜ መፍትሄዎች ናቸው? ለዚህም የገንዘብ? ተግባራቱን ለመፈጸም ቴክኒካዊ አቅም አለን ወይ?




ምስል 10: የችግር ዛፍ

ይህ ውስብስብ ከ2 እስከ 3 ሰዓት የሚፈልግ ዘዴ ነው፡፡

ቁሳቁስ:

ትልልቅ ወረቀቶች፣ የተለይየ ቀለም ያላቸው እስክርቢቶዎች፣ ቾክ

## 3.5 የግብረ መልስ እና የማህበረሰብ የድርጊት መርሀ ግብር ማዘጋጀት

በግብረ መልስ ስብሰባው ወቅት፣ አሳታፊ የገጠር ግምገማ ውጤቶች ለተመረጡ የማህበረሰቡ አባላት ይቀርባሉ፤ ይህም ለመወያይት፣ ለማረጋገጥ እና የተሳሳቱ ውጤቶችን ለማስተካከል ይረዳል። የግብረ-መልስ ውይይቶች አሳታፊ እቅድ ክፍል ግዜን ሊያጠናቅቅ እና የማህበረሰብ የድርጊት መርሀ ግብርን ለማዘጋጀት፣ የማህበረሰብ ለውጥን ለመተግበር ፍኖተ ካርታውን መለየት እና ምን እንደሚሰራ፣ በማን፣ እንዴት እና እስከመቼ እንደሚተገበር ማወቅ ያስፈልጋል። የማህበረሰብ የድርጊት መርሀ-ግብር ማህበረሰቡ ማሳካት የሚፈልጋቸን ነገሮች፣ ምን አይነት ተግባራት ያስፈልጋሉ፣ ምን አይነት ሀብቶች እና መቼ ያስፈልጋሉ (ገንዘብ፣ ሰዎች እና ቁሳቁሶች)። የማህበረሰብ የድርጊት መርሀ-ግብር የአሳታፊ የገጠር ግምገማን ወደ መዋቅራዊ አመክንዮ፣ አርብቶ አደሮች የተገኙ የመፍትሄ ስትራቴጂዎችን እና ትንንሽ ፕሮጀቶችን መተግበር፣ መቆጣጠር እና መገምገም እንዲችሉ የማህበረሰብ ድርጊት መርሀ-ግብርን የማጣቀሻ ይተረጉማል።

የማህበረሰብ የድርጊት መርሀ-ግብሩን ለማጠናቀቅ የሚረዱ ደረጃዎች

1. የማህበረሰብ መረጃዎችን መገምገም እና መመርመር። የድርጊት መርሀ-ግብር ለማዘጋጀት፣ ብዙ ዋጋ ያላቸው መረጃዎች ተሰብስበው ተደራጅተው አንድ ጉዳይ ወይም ስትራቴጂ ውሳኔ ላይ ለመድረስ አስተዋጾ አድርገዋል። ይህም ውጤቱን ለማህበረሰብ የድርጊት መርሀ-ግብር ጥቅም ላይ እንዲውል ያስችላል።
2. ከአጋሮች እና የማህበረሰብ ባለ-ድርሻ አካላት እንዲሁም ነዋሪዎች ጋር በጋራ በመሆን የማህበረሰብ ግብረ-መልስ ግብአቱን መመርመር እና መገምገም። ከማህበርሰቡ የሚሰበሰብ መረጃ በጣም ጠምሚ እና በእቅዱ ውስጥ ምን መፍትሄ መዘጋጀት እንዳለበት አመላካች ነው።
3. የድርጊት መርሀ-ግብሩን በጋራ ለመጻፍ ሰዎችን ይምረጡ። የመጻፍ ሂደቱ በአንድ ወይም በሁለት ሰዎች ሊወሰን ይችላል። እቅዱን የማዘጋጀት ሂደት በትብብር እና በጋራ ሊዘጋጅ ይችላል፤ ጸሀፊዎቹ የድርጊት መርሀ-ግብሩን ወደ ተጻፈ እቅድ ሊተረጉሙት ይችላሉ። ብዙ ጸሀፊዎች የተበጣጠሰ እቅድ ሊስያተካክሉ ይችላሉ።
4. ከማህበረሰብ ግብአት እና ግምገማ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች መለየት። በጣም ጠቃሚዎቹ ጉዳዮች በማህበረሰቡ የተለዩ ናቸው፤ እቅዱም ይህንኑ ሊያሳይ ይገባል።
5. ችግሮቹን የሚፈቱ የአካብቢ ለውጦችን ወይም ፖሊሲዎች መለየት። እነዚህ በማህበረሰቡ ውስጥ ጤናማ ለውጥ ማምጣት የሚችሉ የፖሊሲ ወይም የአካባቢ ለውጥ ስትራቴጂዎች ናቸው። ከተሞከሩ መፍትሄዎች ውስጥ መምረጥ የሚልቻ ቢሆንም እቅዱን ለሚያስፈጽሙት ቡድኖች ተገቢው እና መተግበር የሚቻለው የትኛው እንደሆነ መምረጥ ያስፈልጋል።
6. ለውጦቹን ወይም ፖሊሲዎቹን በስኬት ለመተግበር የሚገጥሙ ችግሮች እና እንቅፋቶች የትኞቹ እንደሆኑ መለየት። የውሳኔው አካል ውጤታማ እና መተግበር የሚችል መፍትሄዎችን በመተግበር ሂደት ውስጥ መሰናክሎችን መመርመር ነው። ለምሳሌ፣ መፍትሄዎቹን ውጤታማ በማድረግ ሂደት ውስጥ ያሉ መሰናክሎች፣ በነዋሪው ማህበረሰብ እና በድርጊት መርሀ-ግብሩ አዘጋጆች መካከል ያለ የባህል እና ቋንቋ ልዩነት ሊሆን ይችላል። በዚህ ግዜ፣ የድርጊት መርሀ-ግብሩን የሚያዘጋጁት ቡድኖች ስትራቴጂያቸው ለማህበረሰቡ ባህሎች እና ቋንቋዎች የተመቸ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።
7. የአካብቢ ለውጡን ለማረጋገጥ ጠቃሚ ሀብቶችን መለየት። የማህበረሰብ የድርጊት መርሀ-ግብርን የሚተገብሩ ግለሰቦችን አቅሞች፣ ንብረቶች፣ ችሎታዎች፣ ግትታዎች እና ሀላፊነቶች መለየት እና አስፈላጊ የሆኑ የማህበረሰቡን ሀብት እና ንብረት መለየት ቁልፍ ነው።
8. እቅዱን የሚተገብሩ ግለሰቦችን እና የማህበረሰብ አጋሮችን መምረጥ። የማህበረሰብ የድርጊት መርሀ-ግብር ብዙ ሰዎች እና ድርጅቶች ልዩ ሀብቶቻቸውን እና ንብረቶቻቸውን በአስተዋጾነት ማበረከት አለባቸው። በእቅዱ ውስጥ ማን ምን ተግባራትን እና ድርጊቶችን መፈጸም እንዳለበት ማስቀመጥ ያስፈልጋል።
9. ተግባራትን ለመፈጸም የግዜ ገደብ ያስፈልጋል። ግዜ ጠቃሚ ሀብት ስለሆነ ለእቅዱ አፈጻጸም የተለያዩ አጋሮችን አስተዋጾ በግልጽ እና በተጨባጭ ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው። ግልጽ የግዜ ገድብ ማስቀመጥ ማን ምን መስራት እንዳለበት እና መቼ ተግባራቱ መጠናቀቅ እንዳለባቸው ለማስቀመጥ ይረዳል።
10. የቁጥጥር እና የግምገማ ተግባራት፤ ስትራቴጂዎቹን እና ተግባራቱን በመማስኬድ ሂደት ውስጥ የድርጊት መርሀ-ግብሩን እድገት ማወቅ አፈላጊ ነው- በዚህ ወቅት ግምገማ ማከናውን ያስፈልጋል። የማህበረሰብ ድርጊት መርሀ-ግብር መግለጫ ያዘጋጁ። በግምገማ ማትሪክስ ውስጥ የግምገማ እቅዶን ያስቀምጡ እና የማህበረሰብ የድርጊት መርሀ-ግብሩ ውስጥ ያካቱት።

| ግቦች | አላማዎች | ድርጊቶች | አስፈላጊ ሀብቶች | ቁልፍ አመላካቾች | ሀላፊነት | የግዜ ገደብ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

የቃላት ትርጉም:

- ግቦች: ከተወሰነ ግዜ በኋላ ቡድኑ ይሳካሉ ብሎ የሚጠብቃቸው ነገሮች። ግብ አንድ ወይም ከዛ በላይ ተያያዥ አላማዎች አሉት።
- አላማዎች: ግብ እና አላማዎች የተገናኙ ናቸው፤ አላማዎች በግልጽ አረፍተ ነገር የተቀመጡ እና ሊደረስባቸው ይችላል ተብለው የሚታሰቡ ነገሮች ናቸው። የመርሀ-ግብር አላማዎች ውስን፣ የሚለኩ እና ግቦቹ የሚለኩ ወሳኝ ምእራፎች ናቸው። በአንድ ግብ ከአንድ በላይ አላማ ሊኖር ይችላል።
- ድርጊቶች: ግቦችን እና አላማዎችን የሚያሳኩ የተወሰኑ ድርጊቶች ናቸው።
- ሀብቶች: የተቀመጡትን መፍትሄዎች ለመተግበር የሚያስፈልጉ እና ያሉ ሀብቶች ምን ምንድናቸው ( የሰው፣ የገንዘብ፣ አካላዊ፣ ማህበራዊ እና የአካባቢ)
- ቁልፍ ማሳያዎች: አመላካቾቹ ውስን፣ የሚታዩ እና የሚለኩ ሲሆን ለውጡን እና እድገቱን የሚያሳዩ መንሆ አለባቸው፤

## 3.6 ገደቦች እና ስጋቶች

በአስተብባሪዎች የተግባቦት ክህሎት ላይ ከፍተኛ ጥገኝነት አለው፤

- ኳሊታቲቭ ቃለ-መጠይቅን በተመለከተ ባህልን ያማከለ የተግባቦት ክህሎት ግንዛቤ ያስፈልጋል፤
- በአግባቡ ለመተግበር አስቸጋሪ መሆን: አሳታፊ የገጠር ግምገማ ውጤቶች ወዲያው ጥሩ ሊሆኑ አይችሉም ምክንያቱም መድሎ ያለበት፣ አጠራጣሪ እና የማይመች ሊሆን ይችላል።
- አስተባባሪዎቹ እና ማስታወሻ ያዡ የአካባቢውን ቋንቋ የማይችሉ ከሆነ በትርጉም ውስጥ ሊበላሽ እና ሊሳሳት የሚችል ነገር ይኖራል። የአካባቢውን የተግባቦት ሁኔታ የሚያውቁ አፋሮች የዋና እቅድ ቡድኑ አባላት ሊሆኑ ይገባል። አስትርጓሚዎች የተቀጠሩ ከሆነ በእቅድ ወቅት እና በውይይት ወቅት መሳተፍ አለባቸው።

ሀይል ያላቸው ቡድኖች እና ግለሰቦች የበላይነት ሊያሳዩባውቸ የሚችሏቸው አደጋዎች

- ያሉትን ኢ-እኩልነቶች ላለመጨመር የልማት ባለሙያዎች በአካባቢው ያለውን የሀይል ግንኙነት እና በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ማህበራዊ ልዩነቶችን ማወቅ መቻል አለባቸው (የተለያዩ ጎሳዎች፣ የሀብት ቡድኖች፣ ወንዶች/ሴቶች)

የተወሰኑት ማህበራዊ ቡድኖች መገለል

- በእቅድ ሂደት ውስጥ የሴቶች ወይም በእንቅስቃሴ ውስጥ ያሉ አርብቶ አደሮች ሀሳቦች ሳይካተቱ ማለፍ
- አሳታፊ የገጠር ግምገማ  ተግባራትን በአመት ውስጥ መድገም አስፈላጊ ነው።

ስህተት ያለበት መረጃ የመኖር አደጋ

- ማትሪክሱን እና ካርታውን ማየት የእይታ ውጤቱን ዘዴ ለመከታተል ዋነኛ መንገድ ነው። ካርታዎቹ እና ምስሎቹ በራሳቸው ውጤት ናቸው እንጂ የሰዎች ውይይት እና ሀሳቦች ድንገተኛ ውጤቶች አይደሉም።

ያልተለመዱ ሀሳቦችን መጫን

- አንድ አንድ ዘዴዎች ከማህበረሰቡ ማህበራዊ እና ባህላዊ ሁኔታ ጋር አይሄዱም። በአርብቶ አደር አካባቢ ድንበር መሳል ተቀባይነት ላይኖረው ይችላል።
- የፈጠራ አስፈላጊነት (ዘዴዎችን በቦታው ላይ መጠቀም ወይም አዲስ ዘዴዎችን ማፍለቅ)

ግዜ መፍጀት

- ይህም የሴቶችን ተሳትፎ ይቀንሰዋል
- ጥቅሞች ጉዳቶችን ሊበልጡ ይገባል

በክትትል ወቅት ደካማነት

- የተለያዩ የአካባቢ ሰዎች ወይም የመንግስት/ የለጋሾች አጀንዳዎች፤
- የግጭት ወቅት
- ለመሳተፍ ቃል ብቻ መግባት
- አርብቶ አደሮች ከልማት ተጠቃሚነት መገለል ሊከሰት ይችላል የሚለው አመለካከት መከሰት፤

# ስነ-ጽሁፍ

Arnstein, S. R. (1969). A ladder of citizen participation. Journal of the American Institute of planners, 35(4), 216-224.

Chambers, R. (2008). PRA, PLA and pluralism: Practice and theory. The Sage handbook of action research. Participative inquiry and practice, 2, 297-318.

Pretty, J., Guijt, I., Thompson, J., & Scoones, I. (1995). Participatory learning and action: A trainer's guide. IED.

Geilfus, F. (2008). 80 Tools for participatory development: appraisal, planning, follow-up and evaluation. IICA. San Jose, Costa Rica.

Schwedes, S., & Werner, W. (2010). Manual for participatory land use planning facilitators. Ministry of Lands and Settlement and German Technical Cooperation (GTZ), 139-141.

Scoones, I. (1994). Browse ranking in Zimbabwe. RRA Notes 20: 91-94. (87)

Waters-Bayer, A., & Bayer, W. (1994). Planning with pastoralists: PRA and more. A review of methods focused on Africa.

# አባሪ 1: የዋና እቅድ ቡድኖች ሚና እና ተግባሮች

| | |
|---|---|
| ውጤት | ቡድኑ የተለያዩ ሀሳቦችን፣ እውቀቶችን እና የእውነታው አረዳድ የጋራ ውጤት የሆኑ ውጤቶችን ለማሳካት ተሳታፊዎቹን ደግፏል።<br><br>የእቅድ ሂደቱ የስራ ሂደቱን እና ውጤቱን በጥቅል የሚያሳይ እውነታዎቹን፣ ሀሳቦችን፣ ክርክሮችን፣ ከግምት ውስጥ ያስገባ ሆኖ መዘጋጀት አለበት። |
| ዘዴ | • አሳታፊ እቅድ ሂደት<br>• አሳታፊ የቡድን ስራ ዘዴ |
| የመመሪያ ጥያቄዎች | • የተሻለ ውጤት ለማምጣት እራሳችንን እንዴት ማደራጀት እንችላለን?<br>• የሚያነሳሳ፣ ፈጠራ የታከለበት ነገር ግን ትኩረት ያለበት ሂደት  እና የመረጃ ሰነድ ዝግጅት እንዴት ይዘጋጃል? |
| ጠቃሚዎች | • አሳታፊ የእቅድ ዝግጅት ሂደት ለተሳታፊ የማህበረሰቡ አባላት ከባድ፣ አንድ አንድ ግዜም አድካሚ እና አስቸጋሪ ሂደት ነው።<br>• ግዜን መጠበቅ፣ በክብር ማስተብበር እና ትኩረት ያለው ማስታወሻ አያያዝ ጥሩ ውጤት ያስመጣል፧ |
| ሰራተኞች | • የቡድን መሪ:<br>- ዝግጅት እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ግንኙነት<br>- የአቅርቦት እቃ<br>- ምግብ እና ትራስፖርት ማመቻችት<br>- ገንዘብ ማስተዳደር (ገንዘብ፣ አበል)<br>• አሰተባባሪዎች:<br>- የተለያዩ ዘዴዎችን እና ቡድኖችን ማስተባበር<br>- የዘዴዎች ውሳኔን በተመለከተ መወሰን<br>• ማስታወሻ ያዥ:<br>- በክፍለ ግዜው ወቅት አስፈላጊ ቁሶችን ማዘጋጀት<br>- ሰነድ የማዘጋጀት ሀላፊነት አለበት<br>- የወረቀት እና እይታዎችን ማዘጋጀት<br>- አስፈላጊ ከሆነ የማስተባበር ሂደቱን ለመውሰድ ለማከናወን ዝግጁ |

| | |
|---|---|
| ቁሳቁስ | • ረጅም ቡኒ ወረቀት<br>• 25 ጥቁር ማርከሮች፣ 15 በሶስት የተለያዩ ቀለማት<br>• ውጤቱን ለማስቀመጥ እንዲረዳ ካሜራ, ጂፒኤስ፣ የድሮን ምስሎች<br>• በሚያስፈልገው መሳሪያ መሰረት የተፈጥሮ ቁሳቁስ |
| መዘጋጀት ያለባቸው | • የቡድን መሪ: ሚናቸው በቅድሚያ ሊነገራቸው ይገባል፤<br>• ቁሳቁሶቹ ሊቀናጁ ይገባል፤<br>• ለተለያዩ መልመጃዎች ዝርዝር ሊዘጋጅላቸው ይገባል፤<br>• ወደ ማህበረብቡ ቅድመ ጉብኝት ያስፈልጋል! |
| ሰነድ ማዘጋጀት | • ፎቶግራፎች፤ በወርክ ሾፑ ግዜ ማስታወሻ መያዝ፣ በቴፕ መቅዳት፤<br>• ስርአት ማስያዝ እና እርማት |

| | |
|---|---|
| አሳታሚ | የጀርመን አለም አቀፍ የልማት ተራድኦ ድርጅት |
| የተመዘገበ ቢሮ | ቦን እና ኢስችቦርን፣ ጀርመን<br>በደረቅ እና ከፊል ደረቅ በሆኑ ቆላማ የኢትዮጵያ አካባቢዎች (አፋር እና ሶማሌ ክልል) የአፈር መልሶ መቋቋምን ማጠናከር<br>ጂአይዚ ቢሮ<br>ራሀም ህንጻ፣ 4ተኛ ፎቅ<br>ፖስታ ሳጥን ቁጥር 100 009<br>አዲስ አበባ, ኢትዮጵያ<br>ስልክ +251 116629983<br>ፋክስ: +251 115540764<br>giz-aethiopien@giz.de<br>www.giz.de |
| ተወካይ | ዶክተር ኤልሳቤት ቫን ደን አከር<br>የፕሮግራም ማኔጀር<br>በደረቅ እና ከፊል ደረቅ በሆኑ ቆላማ የኢትዮጵያ አካባቢዎች (አፋር እና ሶማሌ ክልል) የአፈር መልሶ መቋቋምን ማጠናከር<br>ኢሜል: elisabeth.akker-van@giz.de<br>ሞባይል: +251 944 739352 |
| | በታህሳስ 2013 |
| ህትመት | በሴንትራል ፕሪንቲንግ ፕረስ ኃላ.የተ.የግ.ማ.፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ |
| ዲዛይን እና ሌይ አውት | እጅግ ዲዛይን ፒኤልሲ፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ |
| የምስል ማብራሪያዎቹ | በሰናይት ወርቁ |
| ጽሁፍ | የጀርመን አለም አቀፍ የልማት ተራድኦ ድርጅት የድርቅ መልሶ መቋቋን መርሀ-ግብር<br>የጀርመን አለም አቀፍ የልማት ተራድኦ ድርጅት ለዚህ ህትመት ይዘት ተጠያቂ ነው |
| | የጀርመን ኢኮኖሚ እና ልማት ትብብር ሚንስትርን በመወከል |
| | ከከብት፣ እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ እና አካባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ባለስልጣን ጋር በመተባበር |